# ጦር አምጣ

በሌብነት ሙያ ፣ የተጨማለቁ
ለተዓማኒነት ፣ ጭራሽ የማይበቁ
አገር ሲያራቁቱ ፣ ካዝና ሲያደርቁ
እግዜሩን አይፈሩ ፣ ይሉኝታን አያውቁ
በትቢት ተነፍተው ፣ ከበሮ እንዳልደቁ
ጃስ ሌባ ሲባሉ ፣ ፈርጥጠው እራቁ
ዘውግን ከለላ አርገው ፣ አየን ሲደበቁ ።

ለባዕድ አሸርጋጅ ፣ ወገኑን የጠላ
ጭንጋፍ የንግዴ ልጅ ፣ የሆነ ደላላ
ዛሬም እንዴ ቀድሞው ፣ እንዲሆን ከለላ
ዮሃንስን ገሎ ፣ አንገቱን ለቀላ
አየነው ለሱዳን ፣ ጭራውን ሲቆላ
መጨረሻው ይህ ነው ፣ ሰው ሲሆን አተላ ።

የህዝብን ጥያቄ ፣ አቃሎ ለናቀ
ስርዓት ላልገዛው ፣ ለተጨማለቀ
ጥጋብ ላሸነፈው ፣ ሞትን ለናፈቀ
እንደፍላጎቱ ፣ ሞቶ ካላለቀ
እሹሩሩ ይብቃ ፣ ስለተደበቀ ።

እንደ ጥጋበኛ ፣ እንደ ኮርማ ወይፈን
ከበሮ ጎትታ ፣ መቀሌ ላይ ስትዘፍን
መልክቱ ግልፅ ነው ፣ አውቀህ አትጨፈን
ካልሞተች ወያኔ ፣ ባገር ሰላም አይሰፍን ።

ፀጋ የመሰለው ፣ ደንቁሮ መፈጠር
በሰማንያ አመቱ ፣ ይላል ደንበር ገተር
እንኳንስ ሊሸፍት ፣ ያቃተው መናገር
ጦር አምጣ እያለ ፣ ቀን ከሌት መፎከር
አንገትን አስግጎ ፣ ሸምቀቆ መቋጠር
መቀበሪያ ጉድጓድ ፣ በራስ እጅ መቆፈር

ወያኔ የሚሏት ፣ ውርዴ ቀበጥባጣ
ከበሮ ጨብጣ ፣ መዝለል እንደፌንጣ
ሞታ እንድትቀበር ፣ ተስካሯ እንዲወጣ
ፀሎት ጀምራለች ፣ እያለች ጦር አምጣ
መች ልምጭ ይቆርጣል ፣ እግዜሩ ሲቆጣ
ያገማታል እንጂ ፣ እንደ እንቁላል ፈርጣ ።

ታዛቢው

December 6, 2018